# የምዝገባ መቀነስ

## በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

### የትናንሽ ት/ቤቶች ውሳኔ/ድንጋጌ ምንድን ነው?

የዴንቨር የትምህርት ቦርድ የትናንሽ ት/ቤቶች ውሳኔ/ድንጋጌን በጁን 2021 አጽድቋታል፣ ይህም ዲስትሪክቱ በዲስትሪክቱ ውስጥ ካሉ የትምህርት ቤት ማህበረሰቦች ጋር በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ እየቀነሰ ያለውን ምዝገባ ለመቅረፍ እንዲሰራ መመሪያ ይሰጣል።

ውሳኔው የDPS ሠራተኞች ለመሸጋገሪያ በአፍ መፍቻ ቋንቋ የመማር-ማስተማር (TNLI) ሞዴልን በመጠቀም ጠንካራ የሁለት ቋንቋ ትምህርትን ጨምሮ ለተማሪዎች ቀጣይነት ያለው መርሃ ግብር አቅርቦትን ለማረጋገጥ በሚያስችሉ መመሪያዎች ለምዝገባ መቀነስ ችግር መፍትሄዎችን ለመፍጠር በማህበረሰብ የሚመራ፣ በዲስትሪክት የሚደገፍ ሂደት እንዲጀምሩ ይጠይቃል።

### የምዝገባ መቀነስ ችግር ምንድን ነው?

በ2014-2020 መካከል፣ DPS በግምት በ5,000 ተማሪዎች ያህል ያነሰ የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች ምዝገባ ነበረው። ይህ አዝማሚያም በሚቀጥሉት አምስት አመታት እንደሚቀጥል ይጠበቃል። ለዚህ መቀነስ ምክንያት ተደርጎ የሚወሰደው የዴንቨር ሥነ-ሕዝባዊ (ዲሞግራፊያዊ) ለውጥ ነው። ለምሳሌ ከ2008 ጀምሮ በዴንቨር ውስጥ የሕፃናት የመወለድ ምጣኔ ቀንሷል። ይህ እውነታ በብዙ የከተማዋ አካባቢዎች ካለው የመኖሪያ ቤት ብዛት መለወጥ ጋር ተዳምሮ እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ልጆች በዴንቨር የህዝብ ትምህርት ቤቶች መመዝገቢያ አካባቢ የሚኖሩ ልጆች እንዲቀንሱ አድርጓል።

### የምዝገባ መቀነስ በት/ቤቶቻችን ላይ ምን ተጽእኖ አለው?

እድሜያቸው ለትምህርት የደረሰ የልጆች ቁጥር እየቀነሰ ሲሄድ፣ በዲስትሪክቱ በሞላ ባሉ ብዙ ት/ቤቶች ምዝገባም እየቀነሰ ነው። ት/ቤቶች ጥቂት ተማሪዎችን ሲመዘግቡ DPS እና ት/ቤቱ ከስቴቱ የሚያገኙት ገንዘብ ይቀንሳል። ይህም ለተማሪዎች ይገባቸዋል ብለን የምናምንባቸውን ሁሉንም ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች በገንዘብ መደገፍ ወይም ማቅረብ መቻልን በጣም አስቸጋሪ ያደርገዋል። ይህ አዝማሚያ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ውስጥ እንደሚቀጥል ተገምቷል።

DPS በዲስትሪክት ለሚተዳደሩ ት/ቤቶች ለተለያዩ ፍላጎቶቻቸው ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ ይሰጣል። ይህም ከሌሎች ምክንያቶች መካከል የትምህርት ምዝገባ የቀነሰባቸው ወይም ሁሉንም የሚፈልጓቸውን መርሃ ግብሮች እና አገልግሎቶች በገንዘብ እና በሠራተኛ ለመደገፍ ከሚያስችላቸው ያነሰ የተማሪዎች ቁጥር ይኖሯቸዋል ተብሎ የሚገመቱ ት/ቤቶችን ጨምሮ ከ215 ተማሪዎች በታች ለሆኑ ት/ቤቶች የሚሰጠውን “የትናንሽ ትምህርት ቤት ድጎማ” እና ተጨማሪ “የበጀት እርዳታን” ሁለቱንም ያካትታል።

### የምዝገባ መቀነስ በት/ቤቶቻችን ላይ ምን ተጽእኖ አለው?

እድሜያቸው ለትምህርት የደረሰ የልጆች ቁጥር እየቀነሰ ሲሄድ፣ በዲስትሪክቱ በሞላ ባሉ ብዙ ት/ቤቶች ምዝገባም እየቀነሰ ነው። ት/ቤቶች ጥቂት ተማሪዎችን ሲመዘግቡ DPS እና ት/ቤቱ ከስቴቱ የሚያገኙት ገንዘብ ይቀንሳል። ይህም ለተማሪዎች ይገባቸዋል ብለን የምናምንባቸውን ሁሉንም ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች በገንዘብ መደገፍ ወይም ማቅረብ መቻልን በጣም አስቸጋሪ ያደርገዋል። ይህ አዝማሚያ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ውስጥ እንደሚቀጥል ተገምቷል።

DPS በዲስትሪክት ለሚተዳደሩ ት/ቤቶች ለተለያዩ ፍላጎቶቻቸው ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ ይሰጣል። ይህም ከሌሎች ምክንያቶች መካከል የትምህርት ምዝገባ የቀነሰባቸው ወይም ሁሉንም የሚፈልጓቸውን መርሃ ግብሮች እና አገልግሎቶች በገንዘብ እና በሠራተኛ ለመደገፍ ከሚያስችላቸው ያነሰ የተማሪዎች ቁጥር ይኖሯቸዋል ተብሎ የሚገመቱ ት/ቤቶችን ጨምሮ ከ215 ተማሪዎች በታች ለሆኑ ት/ቤቶች የሚሰጠውን “የትናንሽ ትምህርት ቤት ድጎማ” እና ተጨማሪ “የበጀት እርዳታን” ሁለቱንም ያካትታል።

### የምዝገባ መቀነስ በት/ቤቶቻችን ላይ ምን ተጽእኖ አለው?

እድሜያቸው ለትምህርት የደረሰ የልጆች ቁጥር እየቀነሰ ሲሄድ፣ በዲስትሪክቱ በሞላ ባሉ ብዙ ት/ቤቶች ምዝገባም እየቀነሰ ነው። ት/ቤቶች ጥቂት ተማሪዎችን ሲመዘግቡ DPS እና ት/ቤቱ ከስቴቱ የሚያገኙት ገንዘብ ይቀንሳል። ይህም ለተማሪዎች ይገባቸዋል ብለን የምናምንባቸውን ሁሉንም ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች በገንዘብ መደገፍ ወይም ማቅረብ መቻልን በጣም አስቸጋሪ ያደርገዋል። ይህ አዝማሚያ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ውስጥ እንደሚቀጥል ተገምቷል።

DPS በዲስትሪክት ለሚተዳደሩ ት/ቤቶች ለተለያዩ ፍላጎቶቻቸው ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ ይሰጣል። ይህም ከሌሎች ምክንያቶች መካከል የትምህርት ምዝገባ የቀነሰባቸው ወይም ሁሉንም የሚፈልጓቸውን መርሃ ግብሮች እና አገልግሎቶች በገንዘብ እና በሠራተኛ ለመደገፍ ከሚያስችላቸው ያነሰ የተማሪዎች ቁጥር ይኖሯቸዋል ተብሎ የሚገመቱ ት/ቤቶችን ጨምሮ ከ215 ተማሪዎች በታች ለሆኑ ት/ቤቶች የሚሰጠውን “የትናንሽ ትምህርት ቤት ድጎማ” እና ተጨማሪ “የበጀት እርዳታን” ሁለቱንም ያካትታል።

### ሙሉ የምዝገባ መጠን ያለው ት/ቤት ለምን አስፈለገ?

ሙሉ የምዝገባ መጠን ያለው ት/ቤት ለተማሪዎች ጠንካራ እና ፍትሃዊ የተማሪ እድሎችን ለማቅረብ በቂ የገንዘብ ድጋፍ አለው፣ የሚከተሉትን ጨምሮ፦

- በመደበኛነት መርሐግብር የተያዘለት ሥነ-ጥበብ፣ የሰውነት ማጎልመሻ፣ ሙዚቃ እና/ወይም ሌሎች ተመራጮች።
- ለብዙ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎች ተስማሚ የክፍል እና የቋንቋ ደረጃ ፕሮግራሞች
- ባለተሰጥኦ እና ባለ ችሎታ፣ የልዩ ፍላጎት ትምህርት፣ የሂሳብ እና ማንበብና መጻፍ እገዛዎች በሁሉም ደረጃዎች
- እንደ የትምህርት ቤት አማካሪዎች፣ ሳይኮሎጂስቶች እና/ወይም ሶሻል ወርከሮች፣ እና የእርቅና ማስማማት ልምዶች ሠራተኛ ያሉ የአእምሮ ጤና ድጋፎች።
- ለአስተማሪ እቅድ እና በመረጃ ላይ ለተመሰረቱ የማስተማሪያ ልምዶች የተወሰነ ጊዜ
- ለመምህራን በአንድ የኮርስ ወይም በክፍል ደረጃ መመዘኛዎች እና ግምገማዎች ላይ ማተኮር መቻል

### አንድ ት/ቤት በቂ የተማሪ ቁጥር ካልተመዘገበለት ምን ይከሰታል?

ዝቅተኛ ምዝገባ ያላቸው አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዙ ጊዜ ወጥነት የሌላቸው በምርጫ የሚሰጡ ኮርሶች ይኖራቸዋል፣ ጥራት ባለው የTNLI ፕሮግራም ላይ ተጽእኖ ይኖራል እና የእገዛ እድሎች (ለምሳሌ በማንበብና መጻፍ እና በሂሳብ ተጨማሪ እገዛ) ይኖራቸዋል ወይም ኤክስቴንሽን (እንደ ባለተሰጥኦ እና ባለችሎታ ፕሮግራሞች) ውሱን ይሆናሉ። ዝቅተኛ የምዝገባ

ምጣኔ እና የTNLI ፕሮግራሚንግ ያላቸው ት/ቤቶች ብዙውን ጊዜ የክፍል ደረጃዎችን በማደባለቅ ጥራትን መቀነስ ሊኖርባቸው ይችላል።

**በትምህርት ቤቶች ላይ ለውጦች መቼ ተግባራዊ ይሆናሉ?**

ይህ ሂደት በአንድ ጀምበር አይጠናቀቅም። ራዕዩ አንዳንድ በመሻሻል ሁኔታ ውስጥ ካሉ እና በከፍተኛ የምዝገባ ማሽቆልቆል ምክንያት ቀደም ብለው መዘጋት ከሚኖርባቸው ት/ቤቶች በስተቀር እስከ 2023-24 የትምህርት ዘመን ድረስ ምንም ዓይነት ለውጥ በትምህርት ቤቶች እንዳይከሰት ነው። ማናቸውም ለውጦች ከመተግበራቸው በፊት፣ DPS ተጽዕኖ ለደረሰባቸው ማህበረሰቦች አማራጮችን ለማዘጋጀት ከትምህርት ቤት ሰራተኞች፣ ቤተሰቦች እና ጎረቤቶች ጋር ይሰራል።

**ለመዘጋት የተለዩት የትኞቹ ትምህርት ቤቶች ናቸው?**

ለመዘጋት የተለየ ት/ቤት የለም፤ ለመዘጋትም ሆነ ለመዋሃድ የታሰቡ የት/ቤቶች ዝርዝርም የለም። የምዝገባ መቀነስ ችግር ፈቺ አማካሪ ኮሚቴ የትኛዎቹ ትምህርት ቤቶች መዘጋት ወይም መዋሃድ እንዳለባቸው ለመወሰን ዲስትሪክቱ የሚጠቀምባቸውን መመዘኛዎች/መስፈርቶች ያዘጋጃል።
ይህ ለት/ቤት ሠራተኞች እና ቤተሰቦች ምን ማለት ሊሆን ይችላል?

ትምህርት ቤቶች ለመዋሃድ ወይም ለመዝጋት ከተለዩ በኋላ DPS በሽግግሩ ውስጥ ቤተሰቦችን እና ሠራተኞችን ለመደገፍ ቁርጠኛ ነው። DPS እና ቦርዱ በማናቸውም ለውጦች ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ሠራተኞች ለመደገፍ ያላቸውን ቁርጠኝነት በግልፅ ገልጸዋል። እንዲሁም DPS ትምህርት ቤቶችን የመለወጥ እቅድ፣ የትምህርት ቤት ምርጫ፣ የመጓጓዣ፣ ልዩ ፕሮግራም እና ሌሎች ለቤተሰባች እና ለተማሪዎቻች አስፈላጊ የሆኑ ፍላጎቶች ዙሪያ ለቤተሰቦች ይደግፋል።

**ለውጦቹ ለTNLI እና ለቋንቋ ትምህርት ፕሮግራሞች ምን ትርጉም ይኖራቸዋል?**

DPS በስምምነት ድንጋጌው ላይ ለተዘረዘሩት ህጋዊ ግዴታዎቻችን ቁርጠኛ ሆኖ ይቆያል። ይህ ድንጋጌ ለብዙ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎቻችን የቋንቋ ድጋፍ እና የቋንቋ ትምህርት ፕሮግራሞችን ለማረጋገጥ የሚያስፈልጉንን መስፈርቶች ይዘረዝራል። ለብዙ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎቻችን እና ቤተሰቦቻችን ከፍተኛ ዋጋ እንሰጣለን እናም ሁል ጊዜም ጠንካራ የቋንቋ ትምህርት ፕሮግራሞችን ማቅረባችን ለማረጋገጥ ቁርጠኞች ሆነን እንቀጥላለን። ትምህርት ቤቶች ከተዘጉ ወይም ከተዋሃዱ ለተማሪዎቻችን ጠንካራ የቋንቋ ፕሮግራሞች መኖራቸውን ለማረጋገጥ ከፍተኛ ትኩረት ይደረጋል። ይህ ውይይት ስለመዘጋት እና መዋሃድ የሆነበት ምክንያት የቋንቋ ፕሮግራሞቻችን መደገፋቸውን እና ተማሪዎቻችንን በተሳካ ሁኔታ ማገልገል እና መደገፍ መቻላችን ለማረጋገጥ ነው።

ት/ቤት ከተዘጋ ማእከል-ተኮር የሆኑ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ፕሮግራሞች ምን ይሆናሉ?

በስምምነት ድንጋጌው ሕጋዊ ግዴታዎች እንዳሉብን ሁሉ ማእከል-ተኮር የሆኑ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ፕሮግራሞች ውስጥ ያሉ ተማሪዎቻችን ጥራት ያላቸው ፕሮግራሞች እና የድጋፍ አገልግሎቶች እንዲኖራቸው ለማድረግ የህግ እና የሞራል ግዴታ አለብን። መዘጋቶች ምንም ይሁኑ ምን DPS ሁሉም ማእከል-ተኮር የሆኑ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ፕሮግራሞች ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ጥራት ወዳለው ፕሮግራም የመሸጋገር እድል ያላቸው መሆኑን ያረጋግጣል።

**የቅድመ መደበኛ ትምህርት (ECE) ምዝገባስ በተመሳሳይ ፍጥነት እየቀነሰ ነው?**

የECE ምዝገባ ከአጸደ ሕፃናት-12ኛ ክፍል ምዝገባ የተለየ እና ከአጸደ ሕፃናት-12ኛ የህዝብ ትምህርት ስርዓት በተለየ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግለት ነው። በኮሎራዶ ስቴት ውስጥ የECE ምዝገባ ቀስትና ያለው አይደለም። ECE ለተማሪዎች የግዴታ አይደለም እናም ብዙ ቤተሰቦች ልጆቻቸውን ለECE አያስመዘግቡም። ይህም ማለት ምዝገባው ከአጸደ ሕፃናት-12ኛ ክፍል ምዝገባ በጣም የተለየ ነው። ስለሆነም ECE ለአጸደ ሕፃናት-12ኛ ክፍል ምዝገባ ግልፅ አመላካች አይደለም። በተለምዶ የDPS ECE 4 የአጸደ ሕፃናት ተማሪዎቹን 50% ይወክላል። ባለፉት በርካታ ዓመታት DPS ለተማሪዎች በተለይም ለECE 3 ተማሪዎች የሚቀርቡትን የECE ቦታዎች ቁጥር በመጨመር ረገድ ትልቅ እመርታዎችን አድርጓል። ስለዚህ የECE ምዝገባ በአንፃራዊነት ተመሳሳይ ሆኖ የቀጠለ ወይም ትንሽ ጭማሪ ያለው ቢሆንም ይህ በተማሪ ቁጥር ላይ ያሉ ለውጦችን የሚያንፀባርቅ አይደለም። ተጨማሪ ቦታዎች የመጨመራቸው ውጤት ነው።

**የቻርተር ት/ቤቶች ት/ቤቶችን በማዋሃድ ሂደት ውስጥ ይሳተፋሉ?**

የምዝገባ መቀነስ በዲስትሪክቱ ውስጥ ያሉትን ሁሉም የት/ቤት ዓይነቶች (በዲስትሪክት-የሚመራ፣ የፈጠራ እና የቻርተር) ላይ ተጽዕኖ ያደርጋል። የDPS ቻርተር ት/ቤቶች በሁሉም የDPS ት/ቤቶች ፍትሃዊ በሆነ መልኩ የሚተገበሩ መመዘኛዎችን/መስፈርቶችን ለማውጣት በምዝገባ መቀነስ ችግር ፈቺ አማካሪ ኮሚቴ ውስጥ ተሳታፊ ናቸው። በተጨማሪም ሁሉም የDPS ቻርተር ት/ቤቶች ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች በመሆናቸው ለገንዘብ አጠቃቀማቸው ሙሉ ኃላፊነት አለባቸው። ይህም ማለት በቂ የተማሪ ቁጥር ካልተመዘገበላቸው ተጨማሪ የዲስትሪክት የገንዘብ ድጋፍ አያገኙም። የገንዘብ አጠቃቀም ተጠያቂነት በእያንዳንዱ ቻርተር ት/ቤት እና በዲስትሪክቱ መካከል ላለው ውል ቁልፍ መስፈርት ነው። ስለሆነም አንድ የቻርተር ት/ቤት ጤናማ የገንዘብ አጠቃቀም ከሌለው ላይታደስ ወይም ፈቃዱን እንዲመልስ/ውሉን እንዲያቋርጥ ሊጠየቅ ይችላል።

**የምዝገባ መቀነስ ምክንያቱ ምንድን ነው? ሁሉም የዴንቨር ቤተሰቦች የግል ት/ቤቶችን እየመረጡ ነው ወይንስ ዲስትሪክቱን ለቀው እየወጡ ነው?**

በDPS ት/ቤቶች የሚመዘገቡ ተማሪዎች ቁጥር ለመቀነሱ በርካታ ምክንያቶች አሉ። የመኖሪያ ቤት ዋጋ መጨመር ብዙ ቤተሰቦች ከተማዋን ለቀው እንዲወጡ እንዳደረጋቸው እንደሆነ እናውቃለን። ባለፉት አሥር ዓመታት ውስጥ የወሊድ መጠን ያለማቋረጥ መቀነሱንም እናውቃለን። የእኛ የምዝገባ መረጃም አብዛኞቹ የዴንቨር ቤተሰቦች የDPS ት/ቤቶችን እንደሚመርጡ ያሳያል። ከዴንቨር ተማሪዎች 8% ብቻ በሌሎች የኮሎራዶ ዲስትሪክቶች ይመዘገባሉ፤ እንዲሁም 6.6% ያህሉ በግል ት/ቤቶች ይማራሉ።

**ለዚህ መመዘኛ/መስፈርት ዲስትሪክቱ በአንደኛ ደረጃ እና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች ላይ ያተኮረው ለምንድ ነው?**

የእኛ የምዝገባ መረጃ እንደሚያሳየው ባለፉት አሥር ዓመታት ውስጥ ከፍተኛ የምዝገባ መቀነስ ያጋጠማቸው የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶቻች ናቸው። ይህ መረጃ ደግሞ በሁለተኛ ደረጃ የሚኖረውን መቀንስ ለመገንዘብ ቀዳሚ አመላካች ነው። አነስተኛ ቁጥር ያላቸው የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ወደ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የሚያልፉ ከሆነ እንዲሁ የመለስተኛ ደረጃ ተማሪዎች ቁጥርም ያነስ ይሆናል። በዲስትሪክቱ ውስጥ ከሁለተኛ ደረጃ ይልቅ ቁጥራቸው የበዛ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች አሉን። እናም እነዚህ ት/ቤቶች በምዝገባ ቁጥር መቀነስ ፈተናዎች የበለጠ ተጽዕኖ ደርሶባቸዋል።

**የኮሚቴው ስብሰባዎች ለሕዝብ ክፍት ናቸው?**

የኮሚቴው ስብሰባዎች “የሥራ ክፍለ-ጊዜዎች” ተደርገው የሚወሰዱ እና ቤተሰቦችን እና ወላጆችን፣ አስተማሪዎችን፣ የትምህርት ቤት መሪዎችን እና የዲስትሪክቱን አባላት ለሚወክሉ የኮሚቴ አባላት የታሰቡ ናቸው። የስብሰባ ማጠቃለያዎች በምዝገባ መቀነስ ችግር የመፍታት አማካሪ ኮሚቴ ድረ-ገጽ ላይ የሚለጠፉ ይሆናሉ።

## ለሕዝብ አስተያየት እድሎች አሉ?

አዎ፣ ኮሚቴው መሪ መርሆችን ሲያወጣ እና መስፈርቶቹን ሲያረቅቅ የህዝብ አስተያየት ይቀበላል። መመዘኛዎች/መስፈርቶች ከተዘጋጁ በኋላ የህዝብ አስተያየትም ይኖራል። እነዚህ የአስተያየት እድሎች በምዝገባ መቀነስ ችግር የመፍታት አማካሪ ኮሚቴ ድረ-ገጽ ላይ የሚለጠፉ ይሆናሉ።